2) በኢትዮጵያ ውስጥ ለነገሮች ማመካኛ ማቅረብ እንዴት እንደሚታይ ምሳሌዎችን ስጥ።

3) እውነተኛ ንስሐ የሚገለጸው እንዴት ነው? ይህን እንዴት እንደተመለከትህ ምሳሌዎችን ስጥ።

4) እውነተኛ ንስሐ ከውሸተኛው እንዴት ይለያል? የሚገለጸውስ እንዴት ነው?

5) ጸሎት።

# ትምህርት አራት

ዘፍጥረት 5-9

## እንደኛ ቀን፡- ዘፍ. 5-6፡8

ዛሬ በየትኛውም አቅጣጫ ብንመለከት፥ ክፉንም ደጉንም እናያለን። ባልዳኑትም ሰዎች መካከል እንኳ ቸርነትንና የሚያስደንቁ ታላላቅ ሥራዎችን እንመለከታለን። ሰው በቴክኖሎጂ በኩል ያሳየው ችሎታም የሚደነቅ ነው። ዳሩ ግን ትልቅ ክፋትም መኖሩን እንመለከታለን። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የሚረግፉባቸው ጦርነቶች ይደረጋሉ። ረሃብ፥ የምድር መናወጥና በሽታም በርክቷል። ለመሆኑ ክፉና መልካም ነገሮች፥ ሁለቱም የሚመጡት ከየት ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ በአሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ አራት ምዕራፎች ውስጥ እንደሚገኝ ባለፈው ሳምንት ተመልክተናል። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ፥ ትላልቅ ነገሮችን የመሥራት ችሎታ አለው። ዳሩ ግን በዙሪያችን ያለማቋረጥ የሚከናወነው ክፉ ሥራ፥ ልክ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ ሁሉ፥ የዘመኑም ሰው በፈጣሪ አምላኩ ላይ ለማመፁ ምስክር ነው። ሁላችንም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን የአዳምና ሔዋን ልጆች ብንሆንም፥ በኃጢአት እጅግ ተበላሽተናል።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የእግዚአብሔርን አምሳል በሰው ሕይወት የሚያንጸባርቁትን ነገሮች ዘርዝር።

ለ) በዓለም ውስጥ የኃጢአትን ተጽዕኖ የሚያመለክቱትን ሌሎች ነገሮች ዘርዝር።

ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ውጤቶች ከሆኑት መካከል አንዳንዶቹን ተመልክተናል። የኃጢአቱ ውጤት በፍጥረት፥ በቤተሰብ ግንኙነቶች ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። በባልና በሚስት፥ ወይም በልጆች መካከል የነበረው ሰላም ተናግቷል። ዛሬ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ እስኪጸጸት ድረስ፥ ያ የመጀመሪያ ኃጢአት እንዴት እንደ ተስፋፋ እንመለከታለን።

2ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 5፡6-8 አንብብ። ሀ) በአዳምና በሴት የዘር ሐረግ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ሰዎች ስም ዘርዝር።

ለ) ጸሐፊው የእያንድንዱን ሰው መሞት ደጋግሞ የጻፈው ለምድነው?

ሐ) ስለ ሄኖክ የተለየው ነገር ምንድነው?

መ) የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ሴቶች ልጆች ማንን የሚያመለክቱ ይመስልሃል?

ሠ) እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ያኖረው ገደብ ምንድነው? (6፡3)።

ረ) በዘፍ. 6፡5 የተጠቀሰውን ሁኔታ ከዛሬው ጋር አወዳድር። ልዩነትና አንድነቱ ምንድነው?

ሰ) በዓለም ውስጥ ለሚፈጸመው ኃጢአት የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር?

ሸ) እግዚአብሔር ለዓለም ምን እንደሚያደርግላት ቃል ገባ?

ቀ) ስለ ኖኅ የተሰጠው ምስክርነት ምንድነው?

1. ከአዳም እስከ ኖኅ ያለው የዘር ሐረግ (ምዕ. 5)

በመላው የአሪት ዘፍጥረት እንደሚናገረው፥ በተለያዩ ግለሰቦች የዘር ሐረግ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። ሁለት ዓይነት የዘር ሐረጎች አሉ፡- በመጀመሪያ፥ የአንድን ግለሰብ የዘር ሐረግ አሳይተው የሚያበቁ የዘር ሐረጎች አሉ። ይህንን ባለፈው ሳምንት በቃየን የዘር ሐረግ ውስጥ ተመልክተናል (4፡17-24)። ከዚያ በኋላ ስለ ቃየን የተጠቀሰ ነገር የለም። ስለ ዔሳውና እስማኤል የዘር ሐረጎችም ይህ እውነት ነው።

ሁለተኛው ዓይነት የዘር ሐረግ፥ በአንድ በተወሰነ ግለሰብ በኩል፥ የእግዚአብሔርን የተመረጠ ሕዝብ የዘር ሐረግ የሚያሳይ ነው። ከሴት እስከ ኖኅ የአዳም የዘር ሐረግ አለ። በኋላም የአብርሃምና የዳዊት የዘር ሐረግ ነበር። ዳሩ ግን ዋናው ቁም-ነገር እነዚህ የዘር ሐረጎች ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ጋር የተያያዙ መሆናቸው ነው። ማቴዎስና ሉቃስ ሁለቱም የኢየሱስን የዘር ሐረግ አንዳቸው ከአዳም፥ ሌላው ከአብርሃም፥ እንደተያያዘ ያሳያሉ።

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተሰብህን የዘር ሐረግ እስከምትችለው ድረስ ወደ ኋላ ተመልሰህ ዘርዝር።

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረው ህዝብ የዘር ሐረጉን ማወቅ ለምን ያስፈልገዋል?

በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኙ የዘር ሐረጎች እያንዳንዳቸው በመጠኑ የተለያየ ዓላማ አላቸው። በዘፍጥረት 5 ውስጥ የሚገኘው የዘር ሐረግ ሁለት አበይት ዓላማዎች አሉት። በመጀመሪያ፥ ጸሐፊው በቀጣዩ የዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ቁልፍ ሰው እስከሆነው ኖኅ ድረስ የተመረጠውን የአዳም የዘር ሐረግ ያሳያል። ሁለተኛ፥ ጸሐፊው በአዳምና ሔዋን ውድቀት ምክንያት የመጣውን እርግማን እንደ ቀጠለ ለማሳየት ይፈልጋል። እግዚአብሔር የሞትን ፍርድ ቢሰጣም፥ አዳምና ሔዋን ወዲያውኑ አልሞቱም። በመጨረሻ ግን የሞቱ የፍርድ ቃል ከፍጻሜ ደረሰና አዳምና ዘሮቹ ሁሉ ሞቱ። በዚህ ክፍል ውስጥ፥ ሞት ስምንት ጊዜ ተጠቅሷል። አይሁዶች ሰዎችን በዘር ሐረጋቸው ሲዘረዘሩ፥ ‹ልጅ› የሚለው ‹ዘር› የሚል ፍች ሊሰጥ ስለሚችል፥ የምድርን ዕድሜ ለመቀመር በእነዚህ የዘር ሐረጎች ለመጠቀም አንችልም።

በዘፍ. 5፡1 ጸሐፊው «የእግዚአብሔር ልጅ» ወደነበረው (ሉቃ.3፡38) ወደ መጀመሪያው ሰው ወደ አዳም የኋሊት ያጓጉዘናል። ጸሐፊው ስለ መጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት አፈጣጠር ሊያስታውሰን ይፈልጋል። በእግዚአብሔር አምሳል የነበሩና እግዚአብሔር ለእነርሱ ያዘጋጃቸውን በረከቶች ሁሉ ሊጠቀሙ ይችሉ ነበር። ዳሩ ግን ኃጢአት ይህንን በመለወጥ ርግማንን አስከተለ። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር

አምሳልነቱ የት ደረሰ? ጠፍቶ ይሆን? ወይስ አሁንም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ይሆን የሚሠራው? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል።

የእግዚአብሔር አምሳል ከአዳም ወደ ልጁ እንደተላለፈ ጸሐፊው በግልጽ ያሳያል። የእግዚአብሔርን አምሳል የተቀበለው አዳም፥ አምሳሉን ለልጁ ለሴት አስተላልፎአል። ምንም እንኳ የአምሳሉ አንዱ አካል ሥጋዊ በመሆኑ ሴት አዳምን ቢመስልም፥ ከፊሉ ደግሞ መንፈሳዊ ስለሆነ፥ እንደ አዳም ሁሉ፥ ሴትም ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠት፥ ለማምለክና ህብረት ለማድረግ የሚችልበት መንፈሳዊ ብቃት ነበረው። በውድቀት ምክንያት በሰው ሕይወት የነበረው የእግዚአብሔር አምሳል ቢበላሽም፥ አሁንም አብሮት አለ። ለዚህ ነው ሰው አሁንም ከእንስሳት በላይ የሆነውና እኛም ለሰው ሁሉ ትልቅ አክብሮት መስጠት የሚያሻን። ለዚህም ነው ሰውን መግደል ጥፋት የሚሆነው (9:6 ተመልከት)። እንዲሁም አዳም አንድ ሌላ ውርስ አስተላልፎአል። እርሱም ሞት ነው። ሰውን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፅ የሚገፋፋው የተፈጥሮው ውጤት መንፈሳዊ ሞት ይሆናል። ይህም ሊሻር የሚችለው በእግዚአብሔር በማመንና እርሱን ለማገልገል ራስን አሳልፎ በመስጠት ነው። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአትም ሞት፤ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» (ሮሜ 5፡12) እንደሚለው፥ ሥጋዊ ሞትም አለ።

ከአዳም እስከ ሄኖክ ድረስ፥ የሞቱት ሰዎች ስም ዝርዝር አልተቋረጠም - ሁሉም ሞተዋል። ዳሩ ግን ይህ ዘገባ ሄኖክ በተባለው ሰው ላይ ተቋረጠ። ስለዚህ ሰው ብዙ ነገር አናውቅም። አዲስ ኪዳን እንደ‹ነቢይ› አድርጎ ያቀርበዋል (ይሁዳ ቁ. 14)። ዘፍጥረት ግን ‹አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ› ሰው እንደሆነ ይገልጻል።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ምን ማለት ነው?

ለ) በዛሬው ጊዜ ‹አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገዋል› የምንላቸውን ክርስቲያኖች ባሕርያት ዘርዝር።

ሄኖክ፥ እግዚአብሔር አካሄዳቸውን ከእርሱ ጋር ያደረጉትን ሰዎች እንዴት እንደሸለማቸው የሚያሳይ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን አደረገ ሲል፥ ለእግዚአብሔር በመታዘዝና ከእርሱ ጋር ህብረት በማድረግ ይኖራል ማለቱ ነው። ሄኖክ የእግዚአብሔር ጓደኛ ነበር። የትም ሥፍራ ቢሆን አሳቡ ወደ እግዚአብሔር ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ግልጽ ህብረት እንዲኖረው ይፈልግ ስለነበር፥ ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ፥ ወዲያውኑ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይፈልግ ነበር። ሄኖክ ይህንን ያደረገው ክፋት እየመጠቀ ይሄድ በነበረበት ዘመን ነው። በዚህ ክፋት መካከል፥ ሄኖክ ሌሎች ክፉ ሰዎችን ለመምሰል አልፈለገም ነበር። ሕይወቱ ፍጹም ቅዱስና የተለየ ስለነበር፥ ሞትን እንዳያይ በማድረግ እግዚአብሔር አከበረው። በኋላ ኤልያስ ሞትን ሳያይ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር እንደተወሰደ ሁሉ፥ ሄኖክም በቀጥታ ወደ ሰማይ ተወሰደ።

ሙሴ የሄኖክን ታሪክ በማቅረብ ለእስራኤሎችና ለእኛ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሽልማቶች እንዳሉት ለማሳየት ይፈልጋል። እስራኤልና እኛ፥ ያለንበትን ትውልድ ላለመምሰል ከወሰንንና፥ ሙሉ ለሙሉ እየታዘዝን ከእግዚአብሔር ጋር ለመራመድ ከቆረጥን፥ የሕይወት በረከት ይጠብቀናል። ምናልባት ሞትን ሳናይ በቀጥታ ወደ መንግሥተ-ሰማይ ላንወሰድ ብንችልም፥ የዘላለም ሕይወት ጽኑ የተስፋ ቃል ግን አለን።

5ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዮሐ. 3፡16 ተመልከት። ለሚያምኑ ሰዎች የተሰጠው ተስፍ ምንድነው?

ለ) እንግዲህ እኛ ከሄኖክ ጋር የምንመሳሰለው እንዴት ነው?

ከሄኖክ በኋላ፥ የሞት ዝርዝር ይቀጥላል። የሄኖክ ልጅ ማቱሳላ ከማንም ሰው በላይ ረዥም ዕድሜ ኖሯል - 969 ዓመታት። ማቱሳላ ማለት ‹ እርሱ ከሞተ በኋላ ጥፋት ይደርሳል› ማለት ነው። ምናልባት እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን መምጣት ለሄኖክ ገልጾለት ይሆናል። የኖኅ አባት የነበረው ላሜሕ (ከቃየን ዘር የሆነው ላሜሕ አይደለም)፥ ሕይወት በምድር ላይ ያመጣውን የመከራ ገፈት እየቀመሰ መሆን አለበት። ኖኅ በመወለዱ ምክንያት አንድ ለውጥ እንደሚመጣ ተገነዘበ። በዚያ

በዙሪያው ካለው ክፉ ነገር፥ በተለይም በተረገመችው ምድር ላይ ብርቱ የጉልበት ሥራ ከማከናወን የሚያሳርፍ አንዳች መጽናናት እንደሚመጣ ተስፋ አደረገ። ዳሩ ግን የሚመጣው ብቸኛ መጽናናት የክፉ ሰዎች ከምድር ላይ በጥፋት ውኃ መደምሰስ እንደሆነ ላሜሕ አላወቀም ነበር።

ከጥፋት ውኃ በፊት ሰዎች ለምን እንዲህ የረዘመ ዕድሜ እንደ ነበራቸው አናውቅም። አንዳንዶች ዓለም በጊዜው የተለየች እንደነበረች ያስባሉ። ምናልባት በምድር ዙሪያ ከነበረው የውኃ ቀለበት ሳቢያ፥ ከፀሐይ የሚመጡ ጎጂ ጨረሮች አይደርሱም ይሆናል። በአሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ፥ የሰዎች ዕድሜ ከጥፋት ውኃ በፊት በግዕከላዊ ከነበረበት ከ 900 ዓመታት ከጥፋት በኋላ ወደ 120 ዓመታት ዝቅ ሲል እንመለከታለን። ከዚያም፥ ልክ እንደ ዛሬው በሰለሞን ዘመን የሰዎች ግዕከላዊ ዕድሜ 70 ዓመት ሆኖ ነበር። የሙሴ ትኩረት ግን ሰዎች ምን ያህል ዓመታት እንደኖሩ በመግለጹ ላይ ሳይሆን፥ የአዳም የኃጢአት ውጤት በሆነው የሞት ቅጣት ላይ ነው።

ምንም እንኳ የምንወዳቸው ሰዎች ሲሞቱ ብናዝንና እግዚአብሔርንም ለምን ሕፃናት ወይም ሌሎች ሰዎች እንደሚሞቱ አብዝተን ብንጠይቅም፥ እነዚህ ጥቅሶች ሞት የአዳም የኃጢአት ውጤት እንደሆነ ያስተምሩናል። የዚህ ዓለም ሕይወታችን ከምናልፍበት የሞት ፍርድ ጊዜ ውስጥ አንዱ አካል ነው። ይህ የማያቋርጥ የሞት ሰንሰለት ኢየሱስ እስኪመለስና ልጆቹም በትንሣኤ አካል እስኪላበሱ ድረስ የሚቀጥል ነው። ከዚያ በኋላ ግን ሞት አይኖርም።

2. ከጥፋት ውኃ በፊት በዓለም ስለነበረው ክፋት የተሰጠ ገለጻ (6፡1-8)።

(ዘፍ. 6፡1-8) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለመረዳት እጅግ አዳጋች ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ነው። የክፍሉ አቢይ ትምህርት በእርግጥ ግልጽ ነው። ሰዎች ምድርን ተራብተው እንዲሞሉ የተሰጣቸው ትዕዛዝ መፈጸም በጀመሩ ጊዜ፥ የዚያኑ ያህል ኃጢአትም በምድር ላይ የበለጠ እየተበራከት ሄደ። ይህም ወደ እግዚአብሔር ፍርድ አደረሳቸው። ፍርዱም በመጨረሻው አብዛኛውን ሕዝብ ባጠፋው የጥፋት ውኃ ተገልጿል። የሰዎች ታላቅ ኃጢአት የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍርድ

ያስከትላል። ግን ‹የእግዚአብሔር ልጆች›፥ ‹የሰው ሴቶች ልጆች›፥ እና ‹ኔፊሊም› እነማን ናቸው?

ጸሐፊው በምድሪቱ ውስጥ የነበረውን ታላቅ ክፋት በሁለት መንገዶች ያሳይል።

1. በእግዚአብሔር ወንዶች ልጆችና በሰው ሴቶች ልጆች መካከል የነበረውን ያልተለመደ ግንኙነት ይገልጻል።

የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ሴቶች ልጆች እነማን እንደሆኑ የሚገልጹ አራት አመለካከቶች አሉ፡-

1. አንዳንዶች በኃጢአት የወደቁ መላእክት እንደሆኑ በማሰብ፥ ተፈጥሮአዊ ደረጃቸውን ተላልፈው በምድር ላይ ከሚኖሩ ሴቶች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንደፈጸሙ ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መላእክት አንዳንድ ጊዜ ‹የእግዚአብሔር ልጆች› ተብለው ተጠርተዋል (ኢዮብ 1:6 ተመልከት)። አንዳንድ መላእክት፥ ምናልባትም ከሰይጣን ጋር በመውደቅ፥ እንዴት ተገቢ ሥፍራቸውን እንደተዉ አዲስ ኪዳን ይገልጻል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህ የወደቁ መላእክት እንደ ‹አጋንንት› ሆነው ተገልጸዋል (2ኛ ጴጥ. 2:4፤ ይሁዳ 6-7 ተመልከት)። ለዚህ አመለካከት ትክክል አለመሆን ከሚቀርቡት ማስረጃዎች አንዱ፥ ኢየሱስ መላእክት እንደማያገቡ መናገሩ ነው (ማር. 12:25 ተመልከት)።

2. የእግዚአብሔር ልጆች የሚለው ወደ ፖለቲካ መሪዎች የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በጥንት ዘመን፥ ነገሥታት ወይም የሕዝብ መሪዎች የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ይታሰብ ነበር። ስለሆነም እነዚህ ጥቅሶች የሚያስተምሩት፥ መሪዎች በርካታ ሚስቶች ማግባታቸውን ነው የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ኃጢአታቸውም ፍትወት ሲሆን፥ መሪዎች በወሲባዊ ባሕርያቸው ፍጹም ራሳቸን ለመግዛት አለመቻላቸው ነው።

3. አንዳንዶች የእግዚአብሔር ልጆች የሚለው፥ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ወደ ተመረጡት ወደ ሴት የዘር ሐረግ የሚያመለክት ነው ይላሉ። የሰው ሴቶች ልጆችም ከቃየን የዘር ሐረግ የተገኙ ሴቶች ነበሩ። ስለሆነም፥ ኃጢአቱ ፈርሃ-እግዚአብሔር ያለበት ሐረግ

ከዓለማዊው ጋር በመቀየጡ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ አምልኮ ሊበከል መብቃቱ ላይ ነው ይላሉ። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለመደ ችግር ነበር። አይሁዶች ብዙውን ጊዜ ከአሕዛብ ሴቶች ጋር ይጋቡ ስለነበር፥ በዚህ ምክንያት ለእውነተኛው አምላክ የነበራቸው አምልኮ ተበላሽቷል (መሳ. 3:6-7)።

6ኛ ጥያቄ፡- ይህ በቤተ ክርስቲያንህ አባላት ውስጥ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው? (2ኛ ቆሮ. 6:14 ተመልከት)።

4. አንዳንዶች የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን አመለካከቶች ያቀናጃሉ። በዚህም፥ የሕዝብ መሪዎች ሰይጣን ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው (አጋንንት ሰፍሮባቸው)፥ ሴቶችን ለፍትወተ ሥጋ መመኘት ይዘዋል ይላሉ። ብቸኛው ትኩረታቸው የጋብቻችን ቅድስና በማጥፋት፥ የወሲብ ግንኙነት ለመፈጸም ብቻ ነበር።

የእግዚአብሔር ልጆች እነማን እንደሆኑ አናውቅም። ዳሩ ግን ኃጢአታቸው፥ ልክ እንደ ሔዋን ሁሉ ያተኮረው በሥጋዊ እንጂ በመንፈሳዊ ነገር ላይ አልነበረም። አዩ-ተመኙም። ዛሬ እንደሚስተዋሉ በርካታ ወንዶች ሁሉ እነርሱም፥ በሥጋዊ ውበት ላይ ብቻ በመመርኮዝ ሴቶችን መረጡ። ከመንፈሳዊ መሥፈርቶች አኳያ መርጠው በማግባት፥ ራሳቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ አልፈለጉም።

7ኛ ጥያቄ፡- ይህ ዛሬ በክርስቲያኖችም አካብቢ ሳይቀር እውነት የሆነው እንዴት ነው?

ክፉት ከመጨመሩ የተነሣ፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ቀጣው። በዚህ ጊዜ በሰው ላይ የታዘዙ ሁለት አበይት ፍርዶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር መንፈሱ ከሰዎች ጋር እንዲህ ለረዥም ጊዜ እንዲታገል አልፈለገም። መንፈስ ቅዱስም ከሰው ጋር የነበረው ግንኙነት በአንድ በሆነ መንገድ ተቀየረ።

ሁለተኛ፥ የሰዎች የዕድሜ ርዝመት ተቀየረ። «ዘመኖቹ መቶ ሃያ ዓመት ይሆናሉ» የሚለውን ዓረፍተ ነገር ለመረዳት የሚቻልባቸው ሁለት መንገዶች አሉ። ይህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ማዕከላዊ ዕድሜ 120 ዓመታ እንዲሆን እግዚአብሔር ማወጁን ሊያመለክት ይችላል። ዳሩ ግን ከጥፋት ውኃ በኋላ ሰዎች ከዚህ ዕድሜ በላይ እንደኖሩ

እንመለከታለን። ስለዚህ ይህ እግዚአብሔር ሰውን ከ120 ዓመታት በኋላ በጥፋት ውኃ እንደሚያጠፋ የተሰጠ ትንቢት ይሆናል። እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን ያመጣው ኖኅን ከመረጠ ከ120 ዓመታት በኋላ ነበር። ይህ እግዚአብሔር በቃል-አቀባዩ በኖኅ በኩል፥ ሰዎች ከጥፋት ውኃ በፊት ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው እንዲመለሱ የሰጣቸው የጸጋ ጊዜ እንደሆነ እንመለከታለን።

ኔፊሊም እነማን እንደሆኑ፥ ወይም ከተጠቀሱት የጥንት ኃያላን ጋር አንድ ዓይነት እንደሆኑ አናውቅም (16፡4)። በሙሴ ዘመን፥ የእግዚአብሔር ልጆችና ኔፊሊም ሁለቱም ለእስራኤል ሕዝብ በደንብ የታወቁ ነበሩ። ምናልባትም ኔፊሊም በእግዚአብሔር ልጆችና በሰው ሴቶች ልጆች መካከል የተደረገው ግንኙነት ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱም ያልተለመዱ ዘሮች ሲሆኑ፥ እስራኤላውያን በከነዓን ለመኖር ከመሄዳቸው በፊት በዚያ ይኖሩ ነበር (ዘኁ. 13፡33)። ድንገት እነዚህ ሰዎች አስደናቂና አስቸጋሪ ተግባሮችን በማከናወናቸው በሰው ፊት እንደ ኃያላን የሚታዩ ግዙፎችና ትልቅ ቁመና ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዳንዶች እነዚህ የተጠቀሱት ኃያላን በዘፍጥረት ምዕ. 5 ውስጥ የተገለጹት እንደሆኑ ያስባሉ። ምንም እንኳ በሰዎች ቢከበሩም፥ በመንፈሳዊ ነገር ከእርሱ ጋር ህብረት ስላልነበራቸው፥ እግዚአብሔር አልተደሰተባቸውም ነበር።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጀግኖች አድርገው የሚቆጥሯቸውን ሰዎች ስም ዘርዝር።

ለ) እግዚአብሔርስ ትልቅ አድርጎ የሚቆጥራቸው ይመስልሃል? ለምን?

2. የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ሴቶች ልጆች ጥምረት በምድር ላይ የመጀመሪያው የክፋት ምሳሌ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣው ሁለተኛው ምክንያት የሰው ጠቅላላ ሁኔታ ነበር። እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች በተመለከተ ጊዜ፥ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ተገንዘበ። በተግባራቸው ብቻ ሳይሆን፥ በልባቸውና በአሳባቸው ሁሉ ክፋትን ለማድረግ ወደዱ። የሰውን የልብ ክፋት ከሚያሳዩ እጅግ ጠንካራ ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ይህ

ነው። ሰዎች እራሳቸውን ምንም ታላላቅ እና የሰለጠኑ አድርገው ቢቆጥሩም፥ እግዚአብሔር በተመለከታቸው ጊዜ ግን፥ ልባቸው የከፋ ነበር። የዛሬዋም የእኛዋ ዓለም እንዲሁ ነች።

9ኛ ጥያቄ፡- የምንኖርባት ዓለም ከዚህ ገለጻ ጋር የምትመሳሰለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ለኃጢአት የሚሰጠውን ምላሽ ልብ በል። በቁጣ ብቻ ሳይወሰን፥ አዘኔታም ተሰምቶት ነበር። እግዚአብሔር ‹አዝኗል›። ኃጢአት በምንሠራበት በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔር ያዝናል። ኃጢአት እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ያለውን አገዛዝ እንዲያቆም በቀጥታ የሚቀናቀን ነው። በኃጢአታችን የምንሰቃየው እኛ ብቻ ሳንሆን፥ እግዚአብሔርም ያዝናል። እንዲያውም እግዚአብሔር ሰውን ባይፈጥር ይሻል እንደነበር ተመኝቷል። ኃጢአት ወደ ፍርድ ይመራል። እግዚአብሔር የሰውን የዘመን ርዝመት በመገደብ ፈርዷል። አሁን ግን ዓለሙን ሁሉ፥ ሰውንም ሆነ እንስሳት በሞት ለመቅጣት ቃል ይገባል። እንዲሁም፥ ኃጢአት- አልባ ቢሆንም ከሰው ልጅ ኃጢአት የተነሣ፥ የተቀረው ፍጥረትም ተፈርዶበታል። የኃጢአት ውጤቶች፥ ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት ያልነበራቸውንም ይጎዳሉ።

ዳሩ ግን ከዓለምና ከኃጢአቷ በተቃራኒ የሚራመድ አንድ ሰው ነበር-ኖኅ። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት «ጻጋ» (ወይም ሞገስ) አገኘ ይላል።

10ኛ ጥያቄ፡- የጸጋን ፍቺ ጻፍ።

ኖኅ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጸጋን አገኘ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምንመለከተው፥ ጸጋ ፍርድ ለሚገባቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲሁ የሚሰጥ ስጦታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኖኅ ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት የጸዳ በመሆኑ ከፍርድ እንዳመለጠ አይናገርም። ኃጢአተኛ ነበር። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተመርጦ ስለ ነበር፥ ከፍርድ አምልጧል። ኖኅ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ከዓለም የተለየ ነበር። ጨለማና ኃጢአት በበረከተበት ዓለም ውስጥ፥ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ተመላልሷል።

ብዙ ሰዎች ለሚሠሩት ኃጢአት ምንም ፍርድ የሚጠብቃቸው አየመሰላቸውም። አንዳችም ቅጣት ሳይቀበሉ፥ ኃጢአት ሊሠሩና የፈለጋቸውን ሆነው ሊኖሩ የሚችሉ ይመስላቸዋል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከኖርንበት ሕይወት አኳያ ዋጋ ሊከፍለን ቃል የገባ ፈራጅ ነው። ባንታዘዝና ብናምፅ፥ በዚህና በዘላለማዊውም ሕይወት እግዚአብሔር ይፈርድብናል። በእግዚአብሔር ፊት እራሳችንን ብናዋርድና ለእርሱም በመታዘዝ ብንኖር ግን፥ የሕይወት ተስፋ ተሰጥቶናል።

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ሰዎች እንዴት ለኃጢአት ፍርድ የለም ብለው ያስባሉ?

ለ) የዚህ ማረጋገጫው ምንድነው?

ሐ) እግዚአብሔር ከምንኖረው ሕይወት አኳያ እንደሚፈርድብን ካመንን፥ ይህ የኑሮ ዘይቤያችንን እንዴት ይወስነዋል?

ሁለተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 6፡9-8፡22

የጥንቱ ዓለም ዛሬ እኛ ከምንኖርባት ዓለም ጋር በብዙው መልኩ ተመሳሳይ እንደሆነ ተመልክተናል። በሥልጣኔ በኩል ትልቅ ዕድገት ታይቷል። ዳሩ ግን በምድር ላይ የሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ፥ የሰዎችም ኃጢአት እንዲሁ በረከተ። እግዚአብሔር በሚመለከትበት በየትኛውም አቅጣጫ፥ የሰዎች አሳብና ልብ ክፉ እንደሆነ አየ። ሆኖም በጨለማ ውስጥ ብቻውን የቆመና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ለመሆን የቆረጠ አንድ ሰው ነበር።

12ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 6፡9-8፡22 አንብብ።

ሀ) ጸሐፊው ኖኅን የገለጸው እንዴት ነው? ይህስ ማለት ምን ማለት ነው? (ቁ. 9)።

ለ) በኖኅ ዘመን የዓለም ሕዝቦች የተገለጹት እንዴት ነው?

ሐ) መርከብዋ እንዴት እንደተገለጸች ለማወቅ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ-ቃላት ተመልከት።

መ) ኖኅ ወደ መርከቡ ማግባት የነበረበት ከእያንዳንዱ የእንስሳ ዓይነት ስንቱን ነበር?

ሠ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሱትን ቁጥሮች ዘርዝር፡- የኖኅ ዕድሜ፥ በመርከብ ውስጥ የቆየበት የጊዜ ርዝመት፥ ወዘተ.

ረ) ኖኅ ከመርከቡ እንደወጣ ወዲያውኑ ምን አደረገ?

ሰ) ከጥፋት ውኃው በኋላ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል ምን ነበር?

ሳይንቲስቶች እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ የሚናገረውን ታሪክ እንደተቃወሙ ሁሉ፥ የሰውን ልጅ ስላጠፋው ዓለም አቀፋዊ የውኃ ጥፋት የሚናገረውንም ታሪክ ተቃውመውታል። ሰዎች ለእዚህ ታሪክ ሦስት አበይት ትርጓሜዎችን ያቀርባሉ፡- መጀመሪያ፥ የማያምኑ ሰዎች፥ ይህ በጥንታዊ ሰው የተፈጠረ አፈ-ታሪክ እንደሆነ ያስባሉ። የጥንቱ ዓለም በርካታ ሰዎች የሰውን ልጅ ስላጠፋው ውኃ የሚያውቋቸው ታሪኮች ነበሩዋቸው። በመሆኑም ይህ ታሪክ እንደ ተረት ያለና የግብረ-ገብነት ትምህርት ለማስተማር የታቀደ እንደሆነ ይናገራሉ። ሁለተኛ፥ ሌሎች ደግሞ የጥፋት ውኃ እንደነበረና ዳሩ ግን በተወሰነ ክልል ብቻ ደርሶ ብዙ ጥፋት እንዳስከተለ ያስባሉ። ዓለም-አቀፋዊ ጥፋት አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ «ሰውም ሁሉ ጠፋ» ሲል፥ አንድም ኖኅ በነበረበት አካባቢ ስለ ተፈጸመው ጥፋት፥ ወይም ስለሚያውቃቸው አካባቢዎች ሁሉ እየተናገረ ነው ይላሉ። ወይም ደግሞ አንድ ገበሬ ከትልቅ ጥፋት በኋላ የተረፈ እህል እንኳን ቢኖረው፥ «እህሉ ሁሉ ወደመ» ብሎ እንደሚናገረው፥ ዓይነት ጥፋት እንደደረሰ የሚያመለክት የንግግር ዘይቤ ነው ይላሉ። ሦስተኛ፥ በሌላ ወገን ደግሞ የጥፋት ውኃን ታሪክ እንደተጻፈው ተቀብለው የሚያምኑ አሉ።

ዓለምን ሁሉ ያጥለቀለቀ የጥፋት ውኃ መኖሩን ለመጠራጠር የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለም። ሕይወት ሁሉ፥ ሰውም ሆነ እንስሳ ስለ ጠፋና ተራሮችም ሁሉ ስለ ተሸፈኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውኃው ምድሪቱን ሁሉ እንደሸፈነ በግልጽ ያስተምራል። ክርስቲያን የሆኑ ሳይንቲስቶችም የጥፋት ውኃው በእርግጥ እንደነበረ ለማሳየት፥ በተለያዩ

የዓለም ክፍሎች በምድር ላይ የደረሰውን ታላቅ ጥፋት የሚጠቁሙ ማስረጃዎች ያቀርባሉ። የበረዶ ዘመን የተፈጠረውና ዳይናሶሮችም (በጥንት ዘመን የነበሩ እጅግ ግዙፍ እንስሳት) የጠፉት በዚህ ወቅት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ዳሩ ግን የዘፍጥረት ጸሐፊ ዋንኛ ዓላማ የጥፋት ውኃ እንደነበረ ማረጋገጥ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር እንዴት በኃጢአት ላይ እንደሚፈርድና ለጽድቅም ሽልማት እንደሚሰጥ ማሳየት ነው።

እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምን ዓይነት ሕይወት ነው? እጅግ በከፋውና ለእግዚአብሔር ብቻቸውን የቆሙ በሚመስለው ዓለም ውስጥ ሲኖሩ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ምን ማድረግ አለባቸው? በሕይወታቸው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ለሚሹ ሰዎች ምን ምን ሽልማቶች አሉ? የጥፋት ውኃ ታሪክ የቀረበው እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው።

በማንኛውም ጊዜ ሆነ የትም ቦታ ብንኖር፥ የክርስቲያኑ ቁጥር ሁል ጊዜም አናሳ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ይልቅ በርከት ያሉ ክርስቲያኖች ይኖራሉ፤ ዳሩ ግን ክርስቲያኑ ሁል ጊዜም ዓለምን ለመቃወም በውጊያ ላይ ነው። በመንፈሳዊ ሰልፍ ውስጥ እንኖራለን (ኤፌ. 6፡10-18)።

13ኛ ጥያቄ፡- ማቴ. 24፡30-39 እና 2 ጴጥ. 3፡3-7 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች፥ ኃጢአተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ፍርድ በተመለከተ ስላለው አመለካከት ምን ያስተምራሉ?

እነዚያ የእግዚአብሔር ልጆች ያልሆኑ ሰዎች፥ እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው እንደማይፈርድባቸው በማሰብ፥ ብዙ ጊዜም ይስቃሉ። እኛም ኃጢአት በዓለም ላይ እየበዛ ሲሄድ ስንመለከት፥ እግዚአብሔር ግድ የሌለው እየመሰለን እንሰጋለን። ይሁንና እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ እንደሚፈርድ ይናገራል። አንዳንድ ጊዜ ፈጥኖ ይፈርዳል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲያውም እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ በመዘግየት፥ በቀስታ ይፈርዳል። ዳሩ ግን ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በኃጢአት ሁሉ ላይ የፍርድ ቀን እንደሚመጣ ሁል ጊዜም ማስታወስ አለብን። ይህ በጥፋት ውኃ ታሪክ ውስጥ ታይቷል።

ሙሴ ሁለት አበይት የሰዎች መደቦችን ያነጻጽራል። በመጀመሪያ ጸሐፊው የእግዚአብሔር ሰው ወደሆነው ወደ ኖኅ ይመለከታል። ኖኅ በሦስት መንገዶች ተገልጾአል፡-

1. ‹ጻድቅ› ተብሏል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‹ጽድቅ› የሚለው ቃል ሲጠቀስ ይህ የመጀመሪያው ነው።

14ኛ ጥያቄ፡- የጽድቅን ፍቺና በሕይወትህም ውስጥ እንዴት እንደሚንፀባረቅ ማብራሪያ ጻፍ።

ኖኅ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት እንዳስገዛ ጽድቅ የሚለው ቃል ይገልጻል። እንደገዛ ፍላጎቱ ከመኖር፥ ወይም የዓለምን የአኗኗር ዘይቤ ከመከተል ይልቅ፥ ሕይወቱን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ሁሉ ለመጠበቅ አሳልፎ ሰጠ።

2. ኖኅ ‹ፍጹም› ሰው ተብሎ ተጠርቷል። ይህ ማለት ኃጢአት አልሠራም ነበር ማለት አይደለም። ኖኅ፥ እንደ እኛ ኃጢአተኛ ሰው ነበር። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ አኗኗር የነበረው በመሆኑ፥ ኃጢአት በሚሠራ ጊዜም ወዲያውኑ ንስሐ ይገባ ስለነበር፥ ግንኙነቱ በቶሎ ይስተካከል ነበር። ክርስቲያኖች ኃጢአት የሌለባቸው አይደሉም። ዳሩ ግን ፍጹማን ለመሆን ከፈለግን፥ ከኃጢአታችን ንስሐ በመግባት በፍጥነት እየተመለስን፥ ሁል ጊዜም ሕይወታችንን በንጽሕና ልንጠብቅ ይገባል።

3. ኖኅ ‹አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ›። ኖኅ እንደ ሄኖክ ዓይነት ሰው ነበር። ለረጅም ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግና በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ወሰነ።

የኖኅ ሕይወት ከዓለም ጠቅላላ ሁኔታ ጋር ተነጻጽሯል። ዓለሙ የተበላሸና በጭካኔ የተሞላ እንደነበር ተገልጾአል። ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ግድ አልነበራቸውም፤ ሊታዘዙትም አልፈለጉም። ሰዎች ከእግዚአብሔር ስለሚመጣው ፍርድ ግዴለሾች ሲሆኑ፥ ኃጢአት ይደረጃል። ሰዎች እንዳሻቸው ይኖራሉ። ከዚህም የተነሣ ቤተሰቦችና አገሮችም ሳይቀር ጠፍተዋል።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሌሎች በምድር ላይ እንዳሻቸው ሆነው በሚኖሩበት ወቅት፥ ለኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሆኖ መገኘት ሊከብደው የሚችለው ለምንድነው?

ለ) ለእኛስ ተመሳሳይ ችግር የሚገጥመን እንዴት ነው?

ምንም እንኳን እግዚአብሔር የዓለምን ክፋት ከተመለከተ በኋላ፥ የሰው ልጅ ተፀፅቶ እርሱን እንዲፈልግ ለበርካታ ክፍለ-ዘመናት ቢታገሥም፥ የፍርዱ ጊዜ ደረሰ። እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሁሉ ለማጥፋት ወሰነ። ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ የሚተርፉት። በመጨረሻው፥ ኖኅ ለእግዚአብሔር ለመኖር ያደረገው ውሳኔ ሽልማት አስገኘለት። ጽድቅ የኋላ ኋላ ሽልማትን ያስከትላል።

እግዚአብሔር ለኖኅ በሕይወት ለመኖር ይከተላቸው ዘንድ የሚገባቸውን ዝርዝር መመሪያዎች ሰጠው።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ፥ ኖኅ እግዚአብሔርን እንደታዘዘ የሚጠቅሱትን ክፍሎች ዝርዝር ጻፍ።

ለ) ይህ እግዚአብሔርን ስለ መታዘዝ አስፈላጊነት ምን ያስተምረናል? (ለምሳሌ መርከብ እንዲሠራ የተሰጠውን ትዕዛዝ ባይታዘዝ ኖሮ፥ ኖኅ ምን ይሆን ነበር?)

1. ኖኅ 140 ሜትር ርዝመት፥ 23 ሜትር ስፋትና 13.5 ሜትር ቁመት ያለው መርከብ መሥራት ነበረበት። ይህ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ልብ በል። ከእግር ኳስ ሜዳ የሚበልጥ ርዝመትና ሦስት ፎቆች ካሉበት ቤት የሚልቅ ከፍታ ያለው ነበር። አንድ በር፥ አንድ መስኮትና ሦስት ፎቆች (ደርቦች) ብቻ ነበሩት። ይሁንና እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁሉ ከያይነቱ ጥንድ ጥንድ እንስሳት ለመያዝ ይችል ነበር። ኖኅ ይህን መርከብ ለመሥራት 120 ዓመታት ወስዶበታል።

ይህ ከኖኅ በኩል የጠየቀውን የእምነት ጥንካሬ ልብ በል! ኖኅ የሚኖረው በምድር መካከለኛው ክፍል አካባቢ እንጂ፥ በውቂያኖስ ዳርቻ አለነበረም። ምናልባት ዝናብ የሚባል ነገር አይቶም አያውቅ ይሆናል(እስከዚህ ጊዜ ድረስ ስለ ዝናብ የተጠቀሰ ነገር አልነበረም)።

ደግሞም የውኃ መጥለቅለቅ ልምምድ በፍጹም አልነበረውም። ባለማቋረጥ ለ120 ዓመታት ለመሥራት ትልቅ ትዕግሥትና ጽናት የሚጠይቅ ነበር። በዙሪያው ከሞሉት የጥፋት ልጆች ፈዝ እንደ ገጠመው ጥርጥር የለውም። ዳሩ ግን ስለ ታዘዘና በትዕግሥት ስለ ጸና፥ ድናአል።

17ኛ ጥያቄ፡- ይህ ከእኛ ደኅንነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

18ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጴጥ. 3፡5 አንብብ። በእዚህ ሥፍራ ኖኅ የተጠቀሰው እንዴት ነው?

በአዲስ ኪዳን ኖኅ ‹የጽድቅ ሰባኪ› ተብሎ ተጠርቷል። ዳሩ ኖኅ እንዴት ሰበከ? በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኖኅ እንደ ተናገረ የተመዘገበው ቃል ቢኖር፥ ከነዓንን በረገመ ጊዜ ነበር። ኖኅ ጽድቅን የሰበከው በኑሮ ዘይቤው ነው። እግዚአብሔርን በታማኝነት በመታዘዝና ለእግዚአብሔር ክብር በመኖር፥ ለተመለከቱት ሁሉ የጽድቅን መንገድ አውጇል። ለ120 ዓመታት መርከቡን በታማኝነት መሥራቱ፥ እግዚአብሔር ሊፈርድ እንዳለ ለሁሉም ሰው ምስክር ነበር።

2. ኖኅ እንስሳትን ወደ መርከብ እንዲያስገባ ተነግሮታል። የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል፡- በመጀመሪያ፥ እንስሳቱን ወደ ኖኅ የሚያመጣው እግዚአብሔር ነበር። እንስሳቱን ፍለጋ መሄድ አልነበረበትም (7፡8)። ሁለተኛ፥ እንስሳቱ ከጥፋት ውኃው በኋላ ለመራባት እንዲችሉ፥ ከእያንዳንዱ ዓይነት እንስሳ ወንድና ሴት ወደ መርከቡ መግባት ነበረበት። ሦስተኛ፥ ንጹሕ ከሆኑ እንስሳት (በጎች፥ ፍየሎች፥ ከብቶች፥ ወዘተ.) ከያይነቱ ሰባት መሆን ነበረበት። ይህም የሆነው እነዚህ እንስሳት በኋላ በአምልኮ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚሠዉና እንዲሁም በኖኅና በቤተሰቡ የሚበሉ ስለ ነበሩ ነው። ሕግ በሲና ተራራ ከመሰጠቱ በፊት እንኳ፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የትኛውን እንስሳ ለመሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ተናግሮ ነበር።

ኖኅ ለ120 ዓመታት መርከቡን በትዕግሥት ከሠራ በኋላ፥ እግዚአብሔር ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከቡ እንዲገባ ነገረው። እንስሳቱ ወደ ኖኅ በመምጣት፥ ወደ መርከቡ ከገቡ በኋላ፥ እግዚአብሔር በሩን

ዘጋው። አሁን የጻጋው ዘመን አብቅቷል። እግዚአብሔር ለሰዎች ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው ወደ እርሱ እንዲመለሱ፥ የ120 ዓመታት ዕድል ሰጥቷቸዋል። እነርሱ ግን ከማመን ይልቅ፥ መብላት፥ መጠጣት፥ መጋባት፥ እና መሥራት የመሳሰሉትን የተለመዱ ተግባራት ማከናወናቸውን ቀጠሉ። የፍርድ ቀን ከደጅ እንደቀረበ አልተገነዘቡም ነበር። ከአንድ ሳምንት በኋላ ዝናቡ መጣል ጀመረ። የሚከተለውን ሠንጠረዥ በመመልከት፥ በጥፋት ውኃ ታሪክ ውስጥ የተዘረዘሩትን ጊዜያት ልብ በል።

ወር ቀን ክስተት የፈጀው የቀናት ብዛት

2 10 የኖኅ ወደ መርከብ መግባትና የበሩ መዘጋት 7

2 17 የዝናቡ መጀመር 40

3 27 የዝናቡ ማባራት 110

7 17 መርከቡ የተራራ ጫፍ ነካ 40

8 27 ውኃው ጎደለ 34

10 1 የመርከቡ በደረቅ መሬት ላይ ማረፍ 40

11 11 ኖኅ ቁራውን ላከው 7

11 18 ኖህ ርግብን ሲልካት የወይራ ቅጠል ይዛ ተመለሰች

11 25 ለኖህ ዳግመኛ ርግብን ሲልካት ሳትመለስ በዚያው ቀረች።

12 17 ውኃው ከምድር ላይ ቀለለ 14

2 27 ኖኅ ከመርከቡ በመውጣት ለእግዚአብሔር የምሥጋና መሥዋዕት አቀረበ 56

ኖኅና ቤተሰቡ በመርከብ ውስጥ ያሳለፏቸው ቀናት ድምር 377

ኖኅና ቤተሰቡ በመርከብ ውስጥ ከዓመት በላይ ከቆዩ በኋላ ወጡ።

እነርሱም በቱርክና በሩሲያ ዳርቻ በሚገኘው በአራራት ተራራ አካባቢ ነበሩ። ምንም እንኳ አንዳንዶች ይህን መርከብ በዓይናቸው እንዳዩ ቢናገሩም፥ መርከቡ እንደተገኘ የሚጠቁም ግልጽ መረጃ የለም።

የጥፋት ውኃው በደረሰ ጊዜ፥ ከምድር ሁሉ 8 ሰዎች ብቻ ተረፉ። እነዚህም ኖኅና ቤተሰቡ ነበሩ። እንዲሁም በመርከብ ውስጥ ከነበሩ እንስሳት በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ ወድመው ነበር። ከዚህ በኋላ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተከፈተ። እንደ አዳም ሁሉ፥ ኖኅ አሁን በእግዚአብሔር የሚያምንና የሚታዘዝ አዲስ የሰው ዘርን የመጀመር ዕድል ነበረው።

ኖኅ ከመርከቡ እንደወጣ፥ ወዲያው እግዚአብሔርን አመለከ። ከንጹሕ እንስሳት (ለመብልና መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ የሚፈቀዱ) ጥቂቶቹን በመውሰድ፥ ባዘጋጀው መሠውያ ላይ በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ሠዋ። የሚቃጠል መሥዋዕት፥ ለሚያቀርበው ሰው የሚበላው ምንም ነገር ሳይተርፍ፥ እንስሳው በሙሉ በመሠውያ ላይ ለእግዚአብሔር የሚቃጠልበት ነው። ይህ መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ብዙውን ጊዜ የሚቀርብ የአይሁዶች የአምልኮ ዘዴ ነበር። ይህም መሥዋዕት አቅራቢው ለእግዚአብሔር ያለውን ሙሉ መሰጠትና ለነገሮች ሁሉ በእርሱ ላይ ያለውን ፍጹም ጥገኝነት የሚያመለክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ መሥዋዕቱን በመመልከት፥ «እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ» ይላል። በብሉይ ኪዳን፥ ይህ የደስታ መግለጫና በሰው የቀረበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘቱ ምልክት ነው።

እግዚአብሔር በኖኅ መሥዋዕት፥ ለሰው ልጅ ሦስት ነገሮችን እንደሚያደርግ ቃል ገባ፡-

1. ከሰው ልጅ ኃጢአት የተነሣ ዳግመኛ ምድርን ላለመርገም
2. ዳግመኛ ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት በውኃ ላለማጥፋት
3. የዓመቱ ወቅቶች፥ ማለትም ክረምትና በጋ በፍጹም እንደማይቋረጡ ቃል ገባ።

19ኛ ጥያቄ፡- ደኅንነትን በተመለከተ፥ ከጥፋት ውኃ ታሪክ ውስጥ የምንማራቸው አንዳንድ ትምህርቶች ምንድናቸው?

ከጥፋት ውኃው ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል፡-

1. እግዚአብሔርም ጻጋን የተሞላና በጽድቅ የሚፈርድ ዳኛ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቀጣል። አንዳንድ ጊዜ ቅጣቱ ከኃጢአት በኋላ ወዲያው ይፈጸማል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ኃጢአተኛን ለመቅጣት ለተወሰነ ጊዜ ይጠብቃል። በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች በንስሐ እንዲመለሱ ለ120 ዓመታት እንደጠበቀ ሁሉ፥ ዛሬም እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ በመጠበቅ፥ ለሰው ልጆች ያለውን ጸጋ ያሳያል (2ኛ ጴጥ. 3፡8-10)።

2. እንዲሁም የጥፋቱ ውኃ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ያለውን ግዛት ያሳያል። እግዚአብሔር የፈጠረውን ውኃ የፍርዱ መፈጸሚያ አድርጎ ተጠቀመበት። ዛሬም እንደዚሁ፥ እግዚአብሔር የተፈጥሮ ኃይላትን እንደተቆጣጠረ ነው። እነዚህን የተፈጥሮ ኃይላት የሰው ልጆችን በኃጢአታቸው ለመቅጣት ይጠቀምባቸዋል። ዳሩ ግን ዋና ፍላጎቱ ኃጢአተኞች ከኃጢአታቸው ተናዝዘው ወደ እርሱ እንዲመለሱ ነው። እግዚአብሔር፥ «እኔ በክፉ ሰው ሞት የምደሰት ይመስላችኋልን? አይደለም» (ሕዝ. 18፡23 በአዲስ ትርጉም) ይላል።

3. በሰው ልጅ ፊት ያሉት ሁለት አማራጮች ብቻ ናቸው። አንድኛው የሕይወት ምርጫ ሲሆን፥ ሌላኛው ደግሞ የሞት ምርጫ ነው። እኛ አንድም የዳኑት ሰዎች ቤተሰብ ነን፥ አሊያም ወደ ጥፋት የሚሄዱት ወገን ነን። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸው አንድ የደኅንነት መንገድ ብቻ አለ። የራሳችንን የደኅንነት መንገድ ለማዘጋጀት አንችልም። እግዚአብሔር ለኖኅ ምን እንደሚሥራ ነግሮታል። ልክ ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለው እምነት ለሰው ልጆች ሁሉ የደኅንነት መንገድ እንደሆነ ሁሉ፥ መርከቡ ለኖኅና ቤተሰቡ ብቸኛ የደኅንነት መንገድ ነበር። ምንም ያህል ጥሩ ሰው ቢሆን፥ የትም ቢኖር፥ ወይም ምንም ያህል ሀብታም ቢሆን፥ እምነቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ካልሆነ፥ ይህም ሰው ከጥፋት አያመልጥም።

ሌላው የሰዎች ቡድን ደግሞ፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ የሚሉና በእግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ላይ የሚሳለቁ ናቸው። ሁል

ጊዜም የሚበዛው ሕዝብ የዚህ ቡድን አባል ነው። ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸው ስንናገር ሊሳለቁብን ይችላሉ፥ ሕይወታችንን እግዚአብሔርን በሚያስደስት መልክ አቀናጅተን ለመኖር ስንወስን ሊስቁብን ይችላሉ፥ ዳሩ ግን በመጨረሻው ከእግዚአብሔር እጅ የፍርድን ጽዋ ይቀበላሉ።

4. ልንድንና እግዚአብሔርን ልናስደስት ከፈለግን፥ የሚከተሉትን ቃላት ማስታወስ ያሻናል።

በመጀመሪያ፥ እምነት ሊኖረን ይገባል። ይህም እምነት ብቸኛና የደኅንነት መንገድ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን መሆን አለበት። ሁለተኛ፥ ጽድቅ ሊኖረን ይገባል። ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት እየታዘዝን በመመላለስ፥ የእምነታችንን እውነተኛነት ማሳየት አለብን። ሦስተኛ፥ ትዕግሥት ሊኖረን ይገባል። ኖኅ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በትዕግሥት ከእግዚአብሔር ጋር እንደተመላለሰ ሁሉ፥ እኛም በእግዚአብሔር ለመሸለም በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ለእርሱ ታምነን ልንኖር ያሻል።

20ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ ሦስት ቃላት በሕይወትህ ውስጥ እየተገለጹ ያሉት እንዴት ነው?

እግዚአብሔር በምድር ላይ ገና የከፋ ፍርድ እንደሚያመጣ ይናገራል። ይህም ዛሬ የምናያት ምድር በእሳት ተቃጥላ እንደምታልፍ ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡7-10)። ልክ እንደኖኅ ዘመን ሁሉ፥ በዚያን ጊዜም ቢሆን ሰዎች እግዚአብሔር እንደማይፈርድባቸው ያስባሉ። ንስሐ ለመግባት እጅግ እስከሚዘገይም ድረስ፥ ሕይወት እንደተለመደው ይቀጥላል። እኛስ እንደኖኅ ከጥፋቱ እንደምናመልጥ እርግጠኞች ነን?

ሦስተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 9፡1-17 አንብብ።

የሰው ዘር በጥፋት ውኃ በመጥፋቱ፥ አዲስ ዘመን ተጀመረ። በሌላ በኩል ግን፥ የሰው ልጅ አዲስ ልደት አገኘ ለማለት እንችላለን። በሚቀጥለው የሕይወት ምዕራፍ፥ እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን አደረገ። ይህም ከኖኅ ጋር የተገባ ቃል ኪዳን በመባል ይታወቃል።

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቃል ኪዳን የሚለው ቃል ፍቺ ምንድነው?

ለ) እኛስ የምንኖረው በየትኛው ቃል ኪዳን ሥር ነው?

22ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 9፡1-17 አንብብ።

ሀ) እግዚአብሔር ለኖኅ የሰጣቸውን ትዕዛዛት ዘርዝር።

ለ) ከእነዚህ ትዕዛዛት ውስጥ ዛሬ ልንጠብቃቸው የሚያሻን የትኞቹን ይመስልሃል? ለምን?

ሐ) እግዚአብሔር ሰውን መግደል ጥፋት እንደሆነ የተናገረው ለምንድነው?

መ) እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

ሠ) የቃል ኪዳኑ ምልክት ምንድነው?

ለጥናት እንዲያመቸን ዘፍ. 9፡1-17ን በሁለት ክፍሎች ለመክፈል እንችላለን፡-

1. እግዚአብሔር ለአዲሱ ትውልድ መመሪያ እንዲሆኑ ለኖኅ የሰጣቸው ትእዛዛት (9፡1-7)።

እግዚአብሔር ልክ አዳምንና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኋላ እንደባረካቸው ሁሉ፥ ለአዳም ከሰጣቸው የመጀመሪያዎቹ በረከቶች ሁለቱን ለኖኅ ደግሞለታል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ኖኅ ምድርን እንደገና እንዲሞላ አዘዘው። እርሱና ልጆቹ ፍሬያማ እንዲሆኑና እንዲባዙ ተነገራቸው።

ብዙ ክርስቲያኖች፥ በወሊድ ቁጥጥር መጠቀም እንደማይችሉ ለማሳየት ይህን ጥቅስ ይጠቀማሉ። ለአዳምና ሔዋን እንዲሁም ለኖኅና ሚስቱ ምድርን እንዲሞሉ ትዕዛዝ መሰጠቱ እውነት ነው። ዳሩ ግን እስኪ የነበሩበትን ሁኔታ ልብ በል። በምድር ላይ የነበሩ ሰዎች እነርሱ ብቻ ነበሩ። ምድር ባዶዋን በመሆኗ፥ ለሰው ልጅ የሚሆን በርካታ ሥፍራ ነበር። ዛሬ ግን ምድር በሰው ብዛት ተጣባለች። በብዙ አገሮች፥ የሰውን ሕይወት ለማቆየት ከሚኖራቸው የማምረት አቅም በላይ፥ የሰዉ ቁጥር እየበረከተ ሄዷል። ምድር በነዋሪዎችዋ እጅግ እየተጨናነቀችና ገናም በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ውስጥ ቁጥሩ በእጥፍ ሊያድግ እየተቃረበ መሆኑን ስናይ፥ ይህ ትዕዛዝ እንደተፈጸመና የወሊድ

ቁጥጥርም አስፈላጊ እንደሆነ ለመናገር አንችልም ይሆን? እንዲሁም ክርስቲያን ወላጆች እንደ መሆናችን፥ ልጆቻችንን ጣዕም ያለው ሕይወት ለመኖር በሚችሉበት ሁኔታ የማሳደግ ግዴታ አለብን። የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት በሚጨምርበት አገር ውስጥ የምንኖር ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ የሕዝባችንን ቁጥር መጨመር ለመቆጣጠር ምን ማድረግ እንደምንችል ወይም እንዳለብን አትኩረን ማሰብ አለብን። በቤተ ክርስቲያናችን ልንነጋገርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

23ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በወሊድ ቁጥጥር ላይ ቤተ ክርስቲያንህ ያላት አቋም ምንድነው?

ለ) መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን የሚያስተምር ይመስልሃል?

ሐ) ከወሊድ ቁጥጥር በጎና ክፉ ገጽታዎች አንዳንዶቹ ምንድናቸው?

መ) በኢትዮጵያ ውስጥ ይህንን ችግር ለማቋቋም ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ የምትችል ይመስልሃል?

ሁለተኛ፥ እንደአዳም ሁሉ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ የሚገዛበትን ሥልጣን ለሰው ሰጥቷል። ምንም እንኳ በእንስሳት መካከል የሰው ፍራቻ ቢኖርም፥ አሁንም ሰው በእነርሱ ላይ ሥልጣን ነበረው።

እዚህ ላይ በመጀመሪያውና ከውድቀት በኋላ በነበሩት ፍጥረታት መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል ይገባል። አሁን በሰውና በእንስሳት መካከል መፈራራት ይኖራል። ደግሞም ሰው ሥጋ የመብላት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ከጥፋቱ በፊት ሰውና እንስሳት የሚመገቡት ዕፅዋትን ብቻ ነበረ።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር አንድ እገዳ አድርጎ ነበር። ማንኛውም ሰዎች የሚበሉት ሥጋ ከደም ጋር መሆን አይገባውም ነበር። ለእዚህ ምናልባት ሁለት ምክንያቶች ይኖራሉ፡- መጀመሪያ፥ በብሉይ ኪዳን፥ ደም የእንስሳው ሕይወት ምሳሌ ነበር። ሰዎች ለኃጢአታቸው ንጹሑን እንስሳ በራሳቸው ምትክ ሲሠዉ፥ ላገኙት ይቅርታ ምሳሌ ይሆን ነበር (ዘሌ. 17፡11)። ደም ሲፈስስ በተመለከቱ ጊዜ ሁሉ፥ ኃጢአተኞች

በመሆናቸው ጥፋተኞች እንደሆኑና መሞትም እንደሚገባቸው ማስታወስ ነበረባቸው። የእንስሳው በእነርሱ ምትክ መሞት ብቻ ነበር የሚያድናቸው። እንዲሁም ደግሞ፥ ከኃጢአታችን ደኅንነትን የገዛልን የኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፋንታ መሞትና ደሙን ማፍሰስ ነበር።

ሁለተኛ፥ በሙሴ ዘመን የነበረውን የጥንት ሰዎች እምነት ለመቃወም ነበር። የጥንት ሰዎች በእንስሳት ደም ውስጥ የተለየ ኃይል እንዳለ ያምኑ ነበር። ደሙንም ከጠጡ ረዥም ዘመን እንደሚኖሩና እንስሳው የነበረውን ኃይል እንደሚያገኙ ይመስላቸው ነበር። ሕይወትን የሚሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ይህ የተከለከለ ልማድ ሆነ።

ዛሬ ደም መብላት ተገቢ ስለ አለመሆኑ ክርስቲያኖች በአሳብ ይለያያሉ። አንዳንዶች ይህ ሕግ፥ ሕግጋት በሲና ተራራ ላይ ከመሰጠታቸው በፊት ስለ ተሰጠና ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ ስለ ታዘዘ፥ ደም መብላት ለሰው ትክክል አይደለም ይላሉ። ሌሎች ደግሞ፥ ዛሬ ደም ብንበላ ምንም ችግር የለበትም። ይህ የጥንት ሰዎችን የተሳሳተ እምነት ለማረም የተሰጠ ጊዜያዊ ሕግ ነበር ይላሉ። በአዲስ ኪዳን፥ ኢየሱስ ሰውን የሚያረክሰው የሚበላው ነገር ሳይሆን፥ በልቡ ያለው ነገር እንደ ሆነ አስተምሯል (ማር. 7፡14-23)።

24ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በኢትዮጵያ ደም የሚጠጡ ሰዎች እነማናቸው?

ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ደም ስለ መጠጣት ምን ታስተምራለች? ለምን?

ደም መጠጣት ብቻ ሳይሆን፥ ደም ማፍሰስ ወይም ሰውን መግደል ስሕተት ነበር። ሆኖም ከዚሁ በመቀጠል እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው ሁለት ደም የማፍሰስ መንገዶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ አንድ እንስሳ ሰው ከገደለ መጥፋት ነበረበት። እግዚአብሔር እንስሳት ከሰው ሥልጣን በታች እንዲሆኑ ስላደረገ፥ ሰውን የገደለ ማንኛውም እንስሳ በሞት መቀጣት ነበረበት።

ሁለተኛ፥ አንድ ሰው ሌላውን ሰው መግደሉ ጥፋት ነበር። ለእዚህ የተሰጠው ምክንያት ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው። አንድ ሰው ምንም ኃጢአተኛ ቢሆን፥ አሁንም ሰው ስለሆነ፥ የእግዚአብሔርም አምሳል አለው። አንድ ሰው ሌላውን ሰው

በሚገድልበት ጊዜ ያንን ሰው ማጥፋት ብቻ ሳይሆን፥ በዚያ ሰው ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል አለማክበሩ ነው። የገቢያቸው መጠን፥ ወይም ዘራቸው ምንም ቢሆን፥ ሰዎች ሁሉ በእኩል ደረጃ በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ ካመንን፥ ይህ ከእነርሱ ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይገባል። በገንዘብ ወይም በዘር መኩራራቱ እዚህ ግባ የሚሉት ጉዳይ አይደለም። ከመሐይሙ እስከ ሊቁ፥ ከለማኙ እስከ ከበርቴው፥ ከፈረንጁ እስከ አበሻው፥ ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል። ስለሆነም ሁሉም ያ የእግዚአብሔር አምሳል ስላለው፥ ሁሉም እኩል ነው። ከቃየን አመለካከት በተቃራኒ፥ የወንድሞቻችን ጠባቂዎች መሆን አለብን።

25ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ክርስቲያኖች በትክክል ይህን ቢያምኑ፥ በሴቶች፥ በድሆች፥ በአካለ ስንኩላን፥ በባዕድ ሕዝቦች፥ ወዘተ. ላይ የሚኖራቸው አመለካከት እንዴት ይቀየራል?

ለ) ይህን በበለጠ ለመረዳት በቤተ ክርስቲያናችን ምን ማድረግ አለብን?

ሌላውን ሰው በተሳሳተ መንገድ በመቅረብ፥ የዚያን ሰው ሕይወት ለሚያጠፉ ለማንኛውም ሰው፥ እግዚአብሔር ለሰብዓዊ መንግሥት መሠረት የሚሆን መመሪያ ሰጥቷል። እግዚአብሔር የሌላውን ሰው በግዴለሽነት የሚያጠፋውን ሰው እንዲገድሉ በሥልጣን ላይ ለነበሩት ሰዎች መብት ሰጣቸው። ይህ አንድን ሰው ለሞት ስለሚዳርግ አደጋ የሚናገር አይደለም። እግዚአብሔር የሚናገረው ሆን ተብሎ ሕሊናው እያወቀ ስለሚፈጸም ግድያ ነው። ጳውሎስ ይህን የመንግሥት መብት፥ ሰይፉ መታጠቅ ይለዋል (ሮሜ 13፡1-6)።

## 2. እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ቃል ኪዳን (9፡8-17)

እግዚአብሔር አንዳንድ ትዕዛዛትን ለኖኅ ከሰጠ በኋላ፥ አሁን ከእርሱና ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር ቃል ኪዳን ይገባል። እግዚአብሔር ፈጣሪ፥ ወይም ጸጋን የተሞላ፥ ወይም ፈራጅ ብቻ ሳይሆን፥ ቃል ኪዳንም የሚያደርግ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች፥ ከእነርሱ ጋር በሚገባው ቃል ኪዳን ላይ

ይመሠርታል። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው የመጀመሪያ ቃል ኪዳን ነው።

ቃል ኪዳን በሁለት ሰዎች፥ ወይም ቡድኖች፥ ወይም በእግዚአብሔርና በሰው፥ ወይም በሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ቡድኖች ጋር የተለያዩ ቃል ኪዳኖችን አድርጓል። እነዚህን ቃል ኪዳኖች አንድ በአንድ ማወቁ አስፈላጊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ዓይነት ቃል ኪዳኖች አሉ። እነዳንዶቹ ቅድመ-ሁኔታ የሌለባቸው ናቸው። ይህን ስንል እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ከሚቀበሉት ሰዎች ምንም የሚፈልጋቸው የማሚያ ነጥቦች የሉም ማለታችን ነው። እንዲያው ሊባርካቸው የተስፋ ቃል ይሰጣል። ሌላው ቅድመ-ሁኔታ ያለበት ቃል ኪዳን ነው። በእዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በረከቱን የሚያወርደው ሕዝቡ ለተሰጣቸው የቃል-ኪዳን ቅድመ-ሁኔታዎች በመታዘዛቸው ላይ በመመሥረት ነው።

በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ቃል ኪዳኖች አሉ። እነርሱም ከኖኅና ከአብርሃም ጋር እግዚአብሔር በየተራ ያደረጋቸው ናቸው። የሚከተለው ሠንጠረዥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን አበይት ቃል ኪዳኖች ያሳያል፡-

ቃል ኪዳን የማጣቀሻ ክፍል የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች የቃል ኪዳኑ ዓይነት

1. ከኖኅ ጋር የተገባ ዘፍ. 9፡8-17 የሰው ልጆች ሁሉ ቅድመ-ሁኔታ የሌለው
2. ከአብርሃም ጋር ዘፍ. 15፡9-21 አብርሃምና ዘሩ ቅድመ-ሁኔታ የሌለው
3. ሲና ዘጸአት 19-24 እስራኤል ቅድመ-ሁኔታ ያለበት
4. ከዳዊት ጋር የተደረገ 2 ሳሙ. 7፡5-16 ዳዊት ቅድመ-ሁኔታ የሌለው
5. አዲስ ኤር. 31፡31-34 አማኞች ሁሉ ቅድመ-ሁኔታ የሌለው

እግዚአብሔር ለኖኅና ከእርሱ በኋላ ላሉት ሁሉ፥ ከእንግዲህ በፍጹም በጥፋት ውኃ የሰውን ልጅ እንደማያጠፋ ቃል ገብቷል። ቃል ኪዳናቹን ለመጠበቁ ምልክት እንዲሆንም፥ በሰማይ ላይ ቀስተ-ደመና አድርጓል። ቀስተ-ደመና በሚታይበት ጊዜ ሁሉ፥ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰውን በጥፋት ውኃ ዳግመኛ ላለማጥፋት የገባውን ቃል ኪዳን ማስታወስ አለበት። እግዚአብሔር በእነዚህ በሺህ በሚቆጠሩ ዓመታት ሁሉ ቃል ኪዳኑን ጠብቋል። ምንም እንኳ ሰዎችን የገደሉ የክልል የውኃ መጥለቅለቆች ቢኖሩም፥ የሰውን ልጅ በሙሉ ያጠፋ ውኃ ግን አልታየም።

ሆኖም ቀስተ-ደመናው ማስጠንቀቂያም ጭምር መሆን አለበት። በኃጢአተኞች ሁሉ ላይ የሚመጣ አንድ ተጨማሪ ብርቱ ፍርድ ይቀራል። የሚገለጸውም በእሳት እንጂ በውኃ አይደለም። ዓለሙ በሙሉ ይጠፋና አዲስ ሰማይና ምድር ይሠራል (2ኛ ጴጥ. 3፡6-10)።

26ኛ ጥያቄ፤ - እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ካደረገው ቃል ኪዳን ምን ማጽናኛ እናገኛለን?

ዛሬ ምሁራን ‹ለሁሉ የሚሆን› ተብሎ በሚጠራው ዘመን ውስጥ እንኖራለን ይላሉ። ይህም ማለት እግዚአብሔር ከጻድቃን ጋር ብቻ ሳይሆን፥ በጸጋው ከሰው ሁሉ ጋር እየሠራ ነው። ጳውሎስ እንዳለው፥ እግዚአብሔር ለጻድቁም ለኃጥአኑም ዝናብን ይሰጣል (የሐዋ. 14፡17)። በዚህ የሁሉ በሚሆን ጸጋ ዘመን፥ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም እንዲፈርድ በምንፈልገው ዓይነት ሁኔታ አይፈርድም። ብዙውን ጊዜ ጻድቁ ዝቅ ብሎ ተረግጦ፥ ኃጥኡ ግን የክፋት ሥራውን ለማካሄድ ነጻ ሆኖ እንመለከታለን። ፍትሕ-አልበኝነት የሰፈነ ይመስላል። ዳሩ ግን በዚህ ለሁሉ በሚሆን ጸጋ ዘመን የምንተማመንበት ነገር ቢኖር፥ አንድ ቀን በእግዚአብሔር የጽድቅ ወንበር ፊት በምድር ላይ በጽድቅ ለተመላለሱቱ ሽልማቶች እንደሚሰጡና ለኃጢአተኝነትም እውነተኛ ፍርድ እንደሚኖር ማወቃችን ነው። የጥፋት ውኃ ታሪክ ቅጽበታዊ የበረከት ችሮታ ላያስገኝልን ቢችልም፥ ሁላችንንም ለእግዚአብሔር ታማኝነትን እንድናሳይ ሊያስተምረን ይገባል። የፍርድ ቀን

ስለሚመጣ፥ ከፍርዱ ለማምለጥ እንደ ኖኅ የጽድቅ ሕይወት መኖር ያስፈልገናል።

## አራተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 9፡18-29

ክርስቲያኖች ከኃጢአት ጋር ባላቸው ግንኙነት ከሁለት በአንዱ ወገን ይመደባሉ። አንዳንዶች በኃጢአት ለሚወድቁ ሰዎች ምንም ትዕግሥት የላቸውም። ፈራጅ ለመሆን ስንፈጥን፥ ፍርዳችንም ጫን ያለ ነው። ሁላችንም ወደ ኃጢአት የማዘንበል ባሕርይ ያለውና ለውድቀት የተጋለጠ ተፈጥሮ እንዳለን እንዘነጋለን። ምህረት ማድረግ ለእኛ በጣም ከባድ ከሆኑት ድክመቶቻችን አንዱ ነው።

27ኛ ጥያቄ፤- ይህንን ድክመት በቤተ ክርስቲያን ልምምድህ ውስጥ እንዴት ተመልክተኸዋል?

ሌላው የድክመታችን ገጽታ ስለ ኃጢአትና ቅድስና ግዴለሽ መሆን ነው። የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች ኃጢአት እንደሠሩ ብናውቅም ሳይቀጡ በዝምታ በማለፋችን ብቻ የበለጠ መንፈሳውያን የሆንን ይመስለናል። አሊያም ሁላችንም ኃጢአት ከመሥራት የማንታቀብ ስለሆነ፥ ቅድስና የሌለውን ሕይወት መምራት ተገቢ እንደሆነ እናስባለን።

28ኛ ጥያቄ፤- ይህን አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ያየኸው እንዴት ነው?

የዘፍጥረት መጽሐፍ እነዚህ ሁለቱም አመለካከቶች የቱን ያህል ስሕተት እንደሆኑ ያሳያል። እግዚአብሔር የእርሱ ታላላቅ ተከታዮች የነበሩትን ወንዶችና ሴቶች ኃጢአት እንኳን አይሸፍንም። ኖኅ በቤተሰቡ ውስጥ ትልቅ ሐዘን ባስከተለው የስካር ኃጢአት ወደቀ። ዳዊት ዝሙትን ፈጸመ። አብርሃም ዋሸ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን ኃጢአቶች ባያልፋቸውም፥ በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ለልጆቹ ያለውን ምህረት እንመለከታለን። ኃጢአት ምን ያህል የእግዚአብሔርን ልብ እንደሚጎዳና በእግዚአብሔርም እንደሚጠላ ተመልክተናል። ኃጢአት በአዳምና ሔዋን ላይ ፈጣን ፍርድ አምጥቷል፤ የሰውን ልጆች

ያጠፋ የውኃ መጥለቅለቅንም አስከትሏል። ዛሬም ኃጢአት በኖኅ የልጅ ልጅ ላይ ፍርድን እንዴት እንዳመጣ እንመለከታለን።

29ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍ. 9፡18-26 አንብብ።

ሀ) የካም ኃጢአት ምን ነበር?

ለ) አድራጎቱስ እንዲህ በክፉ መንገድ የታየው ለምን ነበር?

ሐ) የተረገመው ማነው? ለምን?

መ) ርግማኑ ምን ነበር?

ሠ) ሙሴ በዘፍጥረት ውስጥ ይህን ታሪክ ለምን የጨመረ ይመስልሃል?

ኖኅ፥ ሴም፥ ካምና፥ ያፌት የሚባሉ ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት። እነዚህ ሦስቱ በዓለም የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ አባቶች ሆኑ። ይህንን በዘፍጥረት 10 ጥናታችን በደንብ እንመለከተዋለን። ሙሴ የሕዝቦችን መመሥረት ከመግለጹ በፊት፥ ከምድር ሕዝቦች መካከል በአንደኛው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ሁኔታ ለማሳየት ፈልጎ ነበር። ይህም ከሁሉ በላይ የእስራኤልን ሕዝብ የሚነካ ነበር። እስራኤላውያን የተሰፋይቱን ምድር ከመውሰዳቸው በፊት በዚያ ይኖር የነበረው የከነዓን ሕዝብ ነበር። ይህ ታሪክ በግልጽ ለመረዳት አዳጋች ቢሆንም ሙሴ ግን ታሪኩን የጻፈበት ዓላማ ከነዓናውያን በምድሪቱ ውስጥ የመኖር መብታቸውን አጥተው ለምን እንዲጠፉ እንደተደረገ ለማሳየት ነው።

‹በትክክል የተፈጸመው ነገር ምን ነበር? ከካም ይልቅ ከነዓን ለምን ተረገመ?› ተብሎ የሚነሣው ጥያቄ ለመመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። የችግሩ መንስዔ ግን የኖኅ የወይን ተክል መትከልና ከዚያም ወይን ጠጅ ጠምቆ በመጠጣት መስከሩ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ወይንን ስለ መጠጣት ቀጥተኛ ተቃውሞ አይሰነዝርም። ወይን የጥንት ሰዎች ዓይነተኛ መጠጥ ነበር። ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል (ዮሐ. 2)። እንዲያውም የወይን ጠጅ የእግዚአብሔር በረከት ምልክት ነበር (መዝ. (104)፡15፤ ኢሳ. 25፡6፤ ዘካ. 8፡12)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወይን ጠጅ

መጥፎ ውጤቶች ያስጠነቅቃል (ምሳሌ 23:29-35፤ ሆሴ. 4:10-11)። በዚህ ታሪካችን ውስጥ አንዳንድ ውጤቶችን እንመለከታለን። ኖኅ ጠጥቶ የሰከረውና እራሱን አዋርዶ ዕራቁቱን የታየው፥ ከወይን ጠጁ የተነሣ ነበር። ይህም የልጅ ልጁን ወደ መረገም መርቶታል። ጌታን በመቅደሱ ያገለግሉ የነበሩ ሰዎች እንዲጠጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር፤ ሌሎችም እንዳይጠጡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር (ዘሌ. 10:9፤ ዘኁ. 6:2-4፤ ምሳ. 31:4-5)። በምጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የወይን ጠጅ በቀጥታ ባይኮነንም፥ ሰክረን እንዳንገኝ ታዘናል (ኤፌ. 5:18)።

ጥሩ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ከሰከረ በኋላ፥ በድንኳኑ ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ። ምንም እንኳ አንዳንዶች አንቀጾች ያመሊብኃጢአት እንደፈጸመ አድርገው ለማመን ቢፈልጉም፥ ኃጢአቱ ካም የአባቱን ዕራቁትነት ካየ በኋላ መሳለቁ እንደሆነ መጽሐፉ የበለጠ እውነትነት ያለው ይመስላል። በመካከለኛው ምሥራቅ ባሕል፥ የአንድን ሰው ዕራቁትነት መሸፈኑት ትልቅ ስድብ ነበር። ብዙውን ጊዜ አንድ ሕዝብ ሌላውን በሚያሸንፍበት ወቅት፥ ባመዛኙ አሸናፊዎቹ የበላይነታቸውን ለማሰየት፥ ሕዝቡን ዕራቁታቸውን ወዴያና ወዲህ እንዲመላለሱ ያደርጉ ነበር። ካም የአባቱን ዕራቁትነት መመልከት ብቻ ሳይሆን፥ ያየውን ለወንድሞቹ በመናገር በአባቱ ላይ የተሳለቀበት ይመስላል። ስለሆነም ዋንኛ ኃጢአቱ በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ የተከነነውን፥ አባቱን ያለ ግከበሩ ነበር። ዶሩ ግን የተቀሩት ሁለቱ የኖኅ ልጆች ሴምና ያፌት፥ ልብስ ይግልበስና ዕራቁትነቱን ባለ መመልከት፥ ለአባታቸው አክብሮትን አሳዩ።

ኖኅ ካም ያደረገውን ነገር ዘሰማ ጊዜ፦ ልጁ ከነዓንን፥ በተዘዋዋሪ መንገድ ካምን ረገመው። ኖኅ በቀጥታ ካምን መርገም ሲገባው፥ ለምን ከነዓንን ረገመው? በእርሱ ላይ ብርካታ እጦለክቶች አሉ። አንዳንዶች በላመሰሉ ልረጅም ቢሆን ከነዓን በኖኅ ላይ በተፈጸመው የኃጢአት ተግባር ተሳትፎአል ይላሉ። በዚህ ምክንያት ተረግሞአል። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አያሳይም። የካምን ጥፋት ብቻ ነው የሚያመልክተው። ካም በሴምና ያፌት በረኪት ውስጥ ያለመጨመሩ፥ እርሱም እንደ ተረገመ ያሳያል። በእርግጥም ከነዓን ጥፋተኛ ነበር

ለሚለው አስተሳሰብ ብቸኛ ድጋፍ የሚሆነው፥ እግዚአብሔር ለአባቱ ኃጢአት በልጁ ላይ ፍርድን እንደማያመጣ የሚናገረው ጥቅስ ነው (ሕዝ. 18:20)።

ስለዚህ ከነዓን በሌላ ምክንያት የተረገመ ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ የአንድ ሰው ዝሪያዎች በቅድመ-አያቶቻቸው ተግባራት ይተባበራሉ የሚል መመሪያ ነበር። ለምሳሌ፥ በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የሌዊ ዘር ለመልከ-ጼዴቅ አሥራት በመክፈሉ ረገድ እንደተባበረና የሰው ልጅ በሙሉ በአዳም ኃጢአት እንደተሳተፈ ይናገራል (ዕብ. 7:4-10፤ ሮሜ 5)። እንደዚሁም ዘፍጥረት፥ የተወሰኑ ግለሰቦችና የዝርያዎቻቸው ዕጣ-ፈንታ በቅድመ-አያቶቻቸው ተግባራት እንደሚወሰን ያሳያል። ሙሴ ይህን ታሪክ የጨመረው ከነዓናውያን ለምን እንደተኮነኑ ለማብራራት ነው። ስለሆነም ይህን ታሪክ ለወደፊት ስለሚፈጸም ነገር እንደተነገረ ትንቢት አድርገን ለመውሰድ እንችላለን። ፍርዱ በዘፈቀደ የተሰጠ አልነበረም፤ ዳሩ ግን ወደ ፊት እንደሚፈጸም እርግጠኛ ለሆነው ነገር በእግዚአብሔር እንደታወጀ ሆኖ ነው። እግዚአብሔር ስለ ከነዓን ሕዝብ የወደፊት ዕጣ በኖኅ በኩል ትንቢት ተናገረ። ልክ ካም ግብረ-ገብነት የጎደለውን ባሕርይ እንዳሳየና ሰውን የማከበር ዝንባሌ እንዳልነበረው ሁሉ፡- የካም ዝርያዎች ማለትም ከነዓናውያን ለእግዚአብሔር ሕግጋት ያላቸውን ጥላቻ ያሳዩ ነበሩ።

በብሉይ ኪዳን፥ በእምነት አባቶች (አእማዳት) ይሰጥ የነበረው እርግማን ወይም በረከት እኛ ሰውን ከምንረግምበት ወይም ከምንባርክበት የተለየ ነበር። የእኛ እርግማን ወይም ባርኮት የሚደረገው በቁጣ ወይም በደስታ ስሜት ሲሆን፥ የልባችንን መሻት ይገልጻል። እርግማኑ ወይም ባርኮቱ ከፍጻሜ ይደርስ ወይም መና ይቀር እንደሆን አናውቅም። በብሉይ ኪዳን ግን፥ መርገሙ አንድ ሰው ለሠራው ክፉ ነገር እንዲፈርድበት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ እውነተኛ ጥሪ ሲሆን፥ በረከት ደግሞ አንድን ሰው እንዲሸልም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ሌላ ዓይነት ጥሪ ነው። እርጉም ወይም ብሩክ መሆን ወደ ፊት እግዚአብሔር የሚፈጽማቸው ትንቢቶች ነበሩ። መርገሞቹ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፍርድ ይታዩ ስለነበር፥ መፈጸማቸውም አይቀሬ ነበር።

የከርሰ-ምድር ተመራማሪዎች የከነዓናውያንን ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ብልሽት የሚያረጋግጥ መረጃ አግኝተዋል። ሙሴ የኦሪት ዘፍጥረትን መጽሐፍ በጻፈ ጊዜ፥ እስራኤላውያን ከነዓናውያንን እንዳይመስሉ ለማስጠንቀቅ ፈልጓል።

30ኛ ጥያቄ፤ - ዘሌ. 18:2-24 አንብብ። በከነዓን ሕዝቦች የተፈጸሙትን ኃጢአቶች ዘርዝር።

በሙሴ ዘመን፥ የከነዓናውያን ባሕል እጅግ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። እግዚአብሔርም እስራኤልን የፍርድ መሣሪያው በመሆን እንድታጠፋቸው አዘዘ። ስለዚያ ጥፋት መፈጸም ሙሴ በዘፍጥረት ውስጥ አንድ ምክንያት ይሰጣል። እርሱም የጠቆመው ችግር፥ ከነዓናውያን ከአባታቸው ከካም፥ የወረሱትን ከግብረ-ገባዊነት የራቀና የግዴለሽነት ዝንባሌ ማንጸባረቃቸውን ነበር። በካም ሕይወት ያቆጠቆጡት የክፉት ዘሮች በከነዓናውያን ልጆቹ መካከል አድገውና ተንሰራፍተው ትልቅ ኃጢአት ሆኑ። እርግጥ ይህንን ለመረዳት ለእኛ የሚያስቸግረን ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

ኖኅ የእርግማንና የበረከትም ትንቢት ተናግሯል። እርግማኑ በከነዓን ላይ ነበር። የወንድሞቹ ባሪያ መሆን ነበረበት። እጅግ ዝቅ ያለ ባሪያ መሆን ነበረበት - የባሪያዎች ባሪያ። ይህ ግን ከነዓን በሥጋዊ ሁኔታ ብቻ የሴምና የያፌት ባሪያ ይሆናል ማለት አይደለም። ይልቁንም ጸሐፊው ስለ ከንዓን፥ ሴምና ያፌት ዝርያዎች እየተናገረ ነው። ይህ ትንቢት ከነዓናውያን የሴም ልጆች በሆኑት አይሁዶች በባርነት በተገዙበት በኢያሱ ዘመን በከፊል ተፈጽሟል። እንዲሁም ከነዓናውያን የያፌት ልጆች በሆኑት በፍልስጤኤማውያንም ተገዝተዋል። እግዚአብሔር ከነዓናውያንን ባሪያ እንዲያደርጓቸውና እንዲያጠፏቸው ቢያዝዛቸውም፥ አይሁዶች ሙሉ ለሙሉ አልታዘዙትም። ስለዚህም ከነዓናውያን ለአይሁዶች የማሰናከያ ዓለት ሆኑባቸው። በመጨረሻ ግን ከነዓናውያን በ146 ዓ.ዓ. በሮማውያን ድል ከተመቱ በኋላ ቀስ በቀስ ከምድር ገጽ ጠፉ።

ኖኅ ሴምና ያፌትን ሁለቱንም ባረካቸው። ሆኖም ሴምን ከመባረኩ በተጨማሪ፥ ኖኅ የሴምን አምላክ ባረከ። ምናልባት ይህ የሆነው፥

የእስራኤላውያን አባት በመሆን፥ የሴም ትውልዶች ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ስለሚኖራቸው ነው። ይህም ግንኙነት ከሁሉም ነገር የሚልቀው በረከታቸው ነበር። ያፌት ሠፊ ግዛት እንደሚያገኝና ከሴም ጋር አብሮ እንደሚኖር ቃል ተገብቶለታል። ይህ የያፌት ሕዝብ እጅግ እንደሚበዛ የተነገረ ትንቢት ይመስላል። እንዲሁም በኢያሱ ዘመን ከአውሮፓ ወደ ከነዓን ለመኖር ስለ መጡት ፍልስጤኤማውያንም ይጠቅሳል። እነርሱም በመጀመሪያ ላይ፥ ከነዓናውያንን በመውጋቱ ተግባር ከእይሁዶች ጋር አብረዋል። የእስራኤል ሕዝብ ጠላት የሆኑት በኋላ ነው።

እዚህ ላይ የሚያሳዝነው ነገር፥ ነጮች ጥቁሮችን በባርነት ስለ ማግዛት እነዚህን ጥቅሶች በዋቢነት መዘከራቸው ነው። ጥቁሮች የካም ትውልዶች ስለሆኑ እግዚአብሔር በባርነት እንዲገዙ አዝዞአል፤ ነጮችም የያፌት ትውልዶች ናቸው ይላሉ። ዳሩ ግን ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። በባርነት እንዲገዙ የተፈረድባቸው የካም ልጆች ሁሉ ኢያቡሴም። ይህ ፍርድ የተሰጣቸው ከነዓንና ዛሬ በምድር ላይ ተሰይተው የማይታወቁት ትውልዶቹ ናቸው።

**31ኛ ጥያቄ፤ ከዚህ ታሪክ ምን ልንማር እንችላለን?**

ከዚህ ታሪክ ውስጥ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ሁለት አበይት መመሪያዎች አሉ። በመጀመሪያ፥ ብዙውን ጊዜ ያወላጆች አመለካከት ወደ ልጆች ማስተላለፉንና እግዚአብሔርም ልጆችን በአባቶቻቸው ኃጢአት በቀጥታ እንደማይቀጣቸው ነው። ዳሩ ግን፥ ልጆች በወደፊት ሕይወታቸው ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውን ዝንባሌ ከወላጆቻቸው ይወርሳሉ። የዘረኝነት ወይም የማህበራዊ ትምክህት ኃጢአቶቻችን በጭሉ ከወላጆቻችን የምንማራቸው ናቸው። በአንድ ትውልድ ውስጥ ጎጂ የሚይሞሰው ነገር፥ በሚቀጥለው ትውልድ ወደ ትልቅ ጥፋት ሊያመራ ይችላል። የቃደሙት ጀርመኖች ፀረ-አይሁዳዊ አመለካከት፥ 6 ሚሊዮን አይሁዶች በልጆቻቸው ወዳለቁበት ወደ ሁለተኛ የዓለም ጦርነት አምርቷል። በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ችግሮችና በአፍሪካ ሁሉ ወደ ጦርነት የሚያመሩ ጎሰኝነቶች መነሻቸው ወላጆች ለልጆቻቸው ያወረሱዋቸው ጎጂ አመለካከቶች ናቸው። ክርስቲያኖች

እንደመሆናችን፥ እነዚህን ክፉ አመለካከቶች ማወቅና ልጆቻችንም እንዳይማሩዋቸው፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመለወጥ መጣጣር አለብን።

32ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ልጆች ከወላጆቻቸው ሊማሩ የሚችሉዋቸውን ክፉ አመለካከቶች ዘርዝር።

ለ) እነዚህ በቤተ ክርስቲያን እንዴት ይታያሉ?

ሐ) እነዚህን አመለካከቶች በማውገዝ፥ ቤተ ክርስቲያን ምን ለማስተማር ትችላለች?

ሁለተኛ፥ በዚህ ታሪክ ውስጥ እኛ የወረስነውን የክፉ ባሕርይ ኃይል ለማየት እንችላለን። ምንም እንኳ ኖኅና ልጆቹ በአዲስ ምዕራፍ ውስጥ ቢኖሩና ክፉ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ቢጠፉም፥ የልባቸው ክፉ መሻት አልተወገደም ነበር። ጳውሎስ (ሥጋ) ወይም (የኃጢአት ተፈጥሮ) የሚለው ነገር በኃጢአት እንዲወድቁ ምክንያት ሆናቸው። ይህ የአዲስ ክርስቲያኖች ችግር ብቻ አይደለም። ምንም ያህል ታላቅ ብንሆንና በክርስትና ዕድሜአችንም ለረዥም ጊዜ ብንቆይ፥ በቀላሉ በኃጢአት ልንወድቅ እንችላለን። በታሪካችን ውስጥ የችግሩ መሠረት ጠጥቶ የሰከረው ኖኅ ነበረ። ሆኖም ኖኅ ጻድቅና እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ የተጠቀመበት ሰው ነበር። ዳሩ ግን ይህ ሰው በኃጢአት ወደቀና በቤተሰቡም ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ደረሰ። ለእዚህ ነው ጳውሎስ የቆምን የሚመስለን ከሆንን፥ እንዳንወድቅ የሚያስጠነቅቀን (1ኛ ቆሮ. 10፡12)። በሳል ክርስቲያኖች አንድን ታላቅ ነገር ለመሥራት እግዚአብሔር ከተጠቀመባቸው በኋላ፥ ብዙውን ጊዜ በኃጢአት ይወድቃሉ። ኖኅ ከጥፋት ውኃው በኋላ ምንም እንደማይደረስበት ሲያስብ፥ ወደቀ። ዳዊትም አገሮችን ሁሉ ከተቆጣጠረ በኋላ ወደቀ። ብዙውን ጊዜ በትዕቢትና በግዴለሽነት ተተብትበን በኃጢአት የምንወድቀው አንድን ታላቅ ነገር እንደሠራን ካሰብን በኋላ ነው። ስለሆነም ከዚህ ልንጠበቅ ይገባናል።

33ኛ ጥያቄ፡- ይህን እውነታ በእራስህም ሆነ በሌሎች በሳል ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው?

ይህ ወደ ኃጢአት የሚገፋፋ ዝንባሌ ራሳችንን ያሳፍረናል። እንዲሁም ሌሎች በኃጢአት ሲወድቁ በምህረት ዓይን እንድናያቸው ሊያነሳሳን ይገባል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት ሥሩን እንዳይሰድ በፍጥነት ልናስወግደው ያሻል። እንደዚሁም ደግሞ ኃጢአተኛው ንስሐ ከገባ በኋላ መራራ እንዳንሆንበት መጠንቀቅ አለብን። እግዚአብሔር እኛን ከከፉ ኃጢአቶቻችን ይቅር ካለን፥ በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች የሆኑንን ሰዎች ኃጢአት ይቅር ማለት የለብንም?

አምስተኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ውይይት እንዲረዳህ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት። እንዲሁም በትምህርት አንድ ውስጥ የሚገኙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎች ከልስ። ከዛሬው ትምህርት፥ መጠየቅ ለሚገቡን ለአራቱ አበይት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምሳሌዎችን አግኝ።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. የጸሎት ጊዜ

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1) ከትምህርት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ አበይት መመሪያዎችን ከልስ።

2) እያንዳንዱ ተማሪ፥ ከመረጣቸው ከአራቱ አበይት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን ለሌሎቹ ያካፍል።

ለ. 1) አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ፥ ነቀፋ የሌለው መሆንና በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጻድቅ መሆን ማለት ምንድነው?

2) ይህ በሰዎች ሕይወት ውስጥ - በቤተሰብ ግንኙነታቸው፥ በሥራቸው፥ በአገልግሎታቸው የሚረጋገጠው እንዴት ነው?

ሐ. 1) ለሰዎች፥ በተለይም ለወጣቶች፥ ብዙዎቹ ሰዎች የክፋትን መንገድ መርጠው ሳለ፥ የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር የሚከብዳቸው ለምንድነው?

2) ቤተ ክርስቲያንህ፥ ክርስቲያን ወጣቶችና አዋቂዎች ዓለምን እንዳይከተሉና የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖሩ ለማስተማር ምን ማድረግ ትችላለች?

መ. 1) የጥፋት ውኃ ታሪክ፥ የደኅንነትና የጥምቀት ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው (1ኛ ጴጥ. 3፡18-22)?

2) የወንጌልን ታሪክ የሚመስለው በምንድን ነው?

3) የኃጥአንን ፍርድና የጻድቃንን ሽልማት በተመለከተ ወንጌል ምን ይላል?

ሠ. 1) ቤተ ክርስቲያንህ በወሊድ ቁጥጥር ላይ ምን አቋም አላት?

2) መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተመለከተ፥ ምን የሚያስተምር ይመስልሃል?

3) ከወሊድ ቁጥጥር በጎና ጎጂ ጎኖቹ የትኞቹ ናቸው።

4) በኢትዮጵያ ውስጥ ይህንን ችግር ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያንህ ምን ለማድረግ የምትችል ይመስልሃል?

ረ. 1) ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠሩ የሚኖረን አመለካከት፥ ከሰዎች ሁሉ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድርብናል?

2) ይህስ የጎሰኝነትን፥ የዘር-መድልዎን (አፓርታይድ)፥ የተማረው ባለተማረው ላይ የሚኖረውን ትዕቢት፥ ድሃና አካለ ስንኩላን የሆኑትን ሰዎች ችግር እንዴት ይፈታል?

3) ክርስቲያኖች አመለካከታቸውን መለወጥ የሚገባቸው በየትኞቹ አስተሳሰቦች ላይ ነው?

ሰ. 1) በክነዓን መረገም ውስጥ የሚገኙ ሁለት አበይት መመሪያዎች ምንድናቸው?

2) እነዚህ ሁለት መመሪያዎች ዛሬ በዓለምና በቤተ ክርስቲያን ዘንድ የሚታዩት እንዴት ነው?

3) ከተሳሳተ አመለካከታቸው እንዲታረሙ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ ትችላለች?

4) ከኖኅ የስካር ታሪክ ውስጥ ለመሪዎች ማስጠንቀቂያ የሚሆነው ምንድነው?

5. ጸሎት።

# ትምህርት አምስት

ዘፍጥረት 10-11፥ ክለሳ

## አንደኛ ቀን፡- ዘፍ. 10

1ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ከኢትዮጵያ ውስጥ የአሥር ጎሳዎችን ስም ዘርዝር።

ለ) የጎሳ ክፍፍል የሚታየው ልምንድነው?

ሐ) ከእነዚህ ክፍፍሎች የሚመነጩ ችግሮች ምንዳናቸው?

የምንኖርባትን ዓለም ስንመለከት፥ ዓለም በተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ተከፋፍላ እናያለን። በሺህ የሚቆጠሩ ቋንቋዎችና በሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች ይስተዋላሉ። ይህም አንዱ ቡድን ሌላውን ወደሚዋጋበት ጎሰኝነት አምርቷል። ይህ የሆነው ለምንድነው? የጎሳዎችና የቋንቋዎች መከፋፈል የተጀመረው የት ነበር? ዘፍጥረት 10 ና 11 የዓለምን የመከፋፈል ምስጢር ይገልጹልናል። በዘፍጥረት 10፥ ሙሴ የተለያዩ የዓለም ነገዶች እንዴት ሦስት ልጆች ከነበሩት ከአንዱ ኖኅ እንደመጡ ያሳያል። የጥቁር ሕዝቦች አባት የሆነው የካም ልጆች፥ የአውሮፓውያንና የእስያውያን አባት የሆነው የያፌት ልጆችና የአይሁዶችና የዐረቦች አባት የሆነው የሴም ልጆች ናቸው።

ዳሩ ግን ዛሬ ዓለም ምንም ያህል በጎሳና በዘር ሐረጎች ብትከፋፈልም፥ በሰው ልጆች መካከል የአንድነትን ስሜት ሊጭር የሚገባው ባሕርይ አለ። አስቀድመን ይህንን አንድነት ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ከመፈጠራቸው አኳያ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ይህንን አንድነት የሰው ልጆች ሁሉ ከአንዱ የኖኅ ቤተሰብ ከመምጣታቸው አኳያ እንመለከታለን። ጳውሎስ ለአቴና አሕዛቦች